በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ
# ክፍል አሥራ ሦስት

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- በቤታችን ስለምትኖረው ቤተ ክርስቲያን ከተማርን የቤተሰቡ አባላት ከዋናዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላቸው ግኑኙነት ምን እንደሚመስል መጠየቅ ያስፈልጋል።
- ሰው ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግኑኙነት እንደ እንግዳ፣ እንደ አድማጭ፣ እንደ ጸሎተኛ ወይም እንደ አገልጋይ ሆኖ ከአራቱ በአንዱ መልክ የሚታይ ነው።

1. <u>ኦርቶዶክሳዊው ሰው - እንደ እንግዳ በቤተ ክርስቲያን</u>

- የተወደዳችሁ ምዕመናን! በቤተ ክርስቲያን ስትገኙ እንደ ልጅ ሆናችሁ ይሰማችኋል? ወይስ ራሳችሁን እንደ እንግዳ ትቆጥራላችሁ?
- በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ራሳችንን እንደ እንግዳ ቆጥረን ወደ ቤተ ክርስቲያን መመላለስ አደገኛ ነው። ምክንያቱም፡-
    - እንግዳ ይጎበኛል እንጂ በውስጡ አይኖርም። እንዲሁ ራሱን እንደ እንግዳ የሚቆጥር ኦርቶዶክሳዊም ተመሳሳይ ስሜት ይኖረዋል፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚኖር ወይም ራሱን የቤተ ክርስቲያን አድርጎ ሳይሆን እንደ እንግዳ ይቆጥራል።
    - እንደ እንግዳ ይሳለማል እንጂ በሌሎች የጸሎት ጊዜያት ተሳትፎ አያደርግም። መንፈሳዊ ጉባኤያትን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ፣ የትምህርተ ሃይማኖት፣ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን… ጥናቶችን መሳተፍ ደስ አያሰኘውም።
    - ወደ ቤተ ክርስቲያንም እንደ እንግዳ በተወሰኑ በዓላት ይገኛል እንጂ በሳምንት ወይም በየዕለቱ በመገኘት መደበኛ ተሳትፎ አያደርግም።

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- በተጨማሪም እንደ እንግዳ ቅዳሴ ሲያልቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት በደጅ ላይ አጭር ጸሎት ያደርጋል እንጂ ልበ አምላክ ዳዊት ‹‹የሠራዊት አምላክ ሆይ፥ ማደሪያዎችህ እንደምን የተወደዱ ናቸው! ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች ትወድዳለች ትናፍቅማለች ልቤም ሥጋዬም በሕያው አምላክ ደስ ተሰኙ። ወፍ ለእርስዋ ቤትን አገኘች፥ ዋኖስም ጫጩቶችዋን የምታኖርበት ቤት አገኘች የሠራዊት አምላክ ንጉሤም አምላኬም ሆይ፥ እርሱ መሠዊያህ ነው። በቤትህ የሚኖሩ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው ለዓለምና ለዘላለምም ያመሰግኑሃል።›› *መዝ 83(84)፡1፡2፡4።* በማለት እንደተናገረው ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ የሆነ የግኑኝነት ሕይወት የለውም።
- ልበ አምላክ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር በቤቱ የመኖርን ጣዕም ስለቀመሰና ስላጣጣመ ‹‹ከአእላፍ ይልቅ በአደባባዮችህ አንዲት ቀን ትሻላለች በኃጥኣን ድንኳኖች ከመቀመጥ ይልቅ፥ በእግዚአብሔር ቤት እጣል ዘንድ መረጥሁ።›› *መዝ 83(84)፡10።* በማለት ዘምሮልናል።
  - እንግዳ ከእንቅልፉ ቀንሶ በማለዳ ከእረፍቱ አጉድሎ በምሽት ወይም በእረፍት ጊዜው ሌሎችን አይጎበኛቸውም። ወደ ቤተ ክርስቲያን በእንግድነት የሚመጣ ሰውም እግዚአብሔር እርሱንና ቤተሰቡን ‹‹እኔ የሚወድዱኝን እወድዳለሁ፥ ተግተው የሚሹኝም ያገኙኛል።›› *ምሳ 8፡17።* በማለት የጋበዘ ቢሆንም በማለዳ በጊዜው አይገኝም ወይም አይደርስም።
- ንጉሥ ዳዊት ከነበረበት ታላቅ ኃላፊነትና ድርሻ ጋር ‹‹በእኩለ ሌሊት አመሰግንህ ዘንድ እነሣለሁ። … በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ…›› በማለት ሳያቋርጥ እግዚአብሔርን ያመሰግን እንደነበርና በቀን ሰባት ጊዜ ማመስገኑም እንዳላስመረረው ነግሮናል። *መዝ 118(119) እና መዝ 5።*

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- የተወደዳችሁ ምዕመናን! ለእናንተና ለቤተሰቦቻችሁ የቤተ ክርስቲያን ደጆች ዘወትር በስፋት የተከፈቱ ናቸው፤ እግዚአብሔርም በእቅፉ ሊያኖራችሁ ፈቃዱ ነውና እንደ እንግዳ ሳትሆኑ ወደ እግዚአብሔር ቀርባችሁ በጸሎት ተነጋገሩ፡፡
- እንግዳ በቤት በሚገኘው ነገር ሁሉ አይጠቀምም፡፡ እንዲሁ በእንግድነት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገሰግሱ ከክርስቶስ አንድነት፣ ከቅዱስ ቁርባን፣ ከንስሐ ሕይወት፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በትርጉሙ ብርሃንነት ከመረዳቱ ራሳቸውን ተሳታፊ አያደርጉም፡፡
- ከቤተክርስቲያን የበዛ መንፈሳዊ ሀብት ሳንሳተፍ እንደ እንግዳ ወዲያው ገብተን ወዲያው አንውጣ!
- ባልንጀሮቹን በምሽት ሊጠይቅ ሄዶ ከእራት በፊት የሚወጣ ሰው ቅዳሴ አስቀድሶ ቅዱስ ቁርባን ሳይቀበል የሚወጣ ሰውን ይመስላል፡፡ በዚሁ መንገድ ራሳችንን እንደ እንግዳ ከቆጠርን በሰሙነ ሕማማት፣ ከኪዳን፣ በአጽዋማትና በፍስክ ጊዜ… ከሚኖሩ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች በረከት እንለያለን፡፡
- ሕይወትን በሰማያዊው አባት በእግዚአብሔር ቤት በቤተ ክርስቲያናችን የሚቀምስ ሁሉ በልበ አምላክ ዳዊት ‹‹ከአእላፍ ይልቅ በአደባባዮችህ አንዲት ቀን ትሻላለች በኃጥኣን ድንኳኖች ከመቀመጥ ይልቅ፥ በእግዚአብሔር ቤት እጣል ዘንድ መረጥሁ፡፡›› ማለት ይቻለዋል፡፡ *መዝ 83(84)፡10፡፡*
  - እንግዳ በመምጣቱ ታላቅ አቀባበል ቢደረግለትም ማንም የሚያውቀው ስለማይመስለው እንደ ባዕድ ራሱን ይቆጥራል፡፡ እንዲሁ በቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን እንደ እንግዳ የሚቆጥሩ ከገቡ ጀምሮ ምቾትና መረጋጋት ስለማይሰማቸው ጥቂት ጊዜ ቆይተው ተሰላችተው በመውጣት ወደ ውጪው (ሥጋው) ዓለም ይሄዳሉ፡፡

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- የተወደዳችሁ ምዕመናን! በቤተ ክርስቲያን እንግዳ ሆነን የሚሰማን፡-
  - ጆሮቻችን የቤተ ክርስቲያንን ዜማ ስላልለመዱ ከልጅነታችንም ጀምሮ ስላልተማር ናቸው፡፡
  - ቀሳውስትና ዲያቆናቱ የሚቀድሱበትን ኢትዮጵያዊውን የግዕዝ ቋንቋ ስላላጠናን ስላልተዋሐደንም
  - ከልጅነታችን ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን የምንከታተልበት ሁኔታ ወጣ ገባ ያለ በመሆኑ
  - ስለ ኃጢአታችን በመናዘዝ የንስሐ ሕይወት ስለማንመራና ኃጢአታችንም በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ግድግዳ ሆኖ ስለጋረደን፡፡ ይህን የኃጢአት ግድግዳ ንስሐ ገብተን ብናፈርሰው በቤተ ክርስቲያን እንግዶች ሆነን አይሰማንም፡፡
  - ባልንጀሮቻችን (ጓደኞቻችን) በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ መንፈሳውያን ሳይሆኑ ከዓለም የሆኑ ዓለማውያን ስለሆኑ
  - በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየኖሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንድንመጣ የሚያበረታቱን አብረውን የሚጸልዩ፣ የሚያስቀድሱ ጓደኞች ስለሌሉን
  - ምናልባት በአጠቃላይ ከቤተ ክርስቲያን ወይም ከአገልጋዮችዋ ጋር በጥሩ ሁኔታ ላይ ስላልሆንን
  - ምናልባት በሌሎች መናፍቃን አዳራሾች መገኘት የጀመርን ሆነን ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጥተን ትምህርትዋን ስንሰማ እንግዶች ሆነን ተሰምቶን
  - ምናልባት ስሜቶቻችን ከዓለም በሆኑ ትምህርቶች የተበከሉ ስለሆኑ፣ ጆሮቻችን በዓለሙ ዘፈን የተሞሉ፣ አእምሮአችን ከመጽሔቶች ወይም ከፊልሞች ያየነውን መጥፎ ነገር ስለሚያስታውሰንና የኃጢአት መከማቻ ቦታ ስለሆንን
  - ምናልባትም ገንዘብ የምናገኝበትን ስልት ብቻ የምናስብ ሆነን ገንዘብ አፍቃሪ በመሆናችን ስለገንዘብ ማሰብን ባለማቋረጥ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ሳይቀር ስለገንዘብ ብቻ ስሌት ስለምንሠራ…

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- የተወደዳችሁ ምዕመናን! በቤተ ክርስቲያን እንግዳ ሆነን የሚሰማን ቢሆንም ቤተ ክርስቲያን ግን አሁንም ፍቅርዋን ትሰጠናለች፡፡
- የተወደዳችሁ ምዕመናን! በቤተ ክርስቲያን እንግዳ ሆነን እንዲሰማን ያደረጉንን ምክንያቶች በማጥናት ከሕይወታችን እናስወግዳቸው፡፡
    - እንግዳ ሌሎችን ለመጎብኘት ሲሄድ ቤተሰቦቹን እንደማይወስድ ሁሉ በቤተ ክርስቲያንም እንደ እንግዳ ራሳቸውን የሚቆጥሩ ሰዎች የቤተሰባቸውን አባላት ይዘው አይገኙም፡፡ ሊረብሹ ወይም መጥፎ ሥነ ምግባር ሊያሳዩ ይችላሉ በማለት ልጆቻቸውን ትተው ወደ ቤተክርስቲያን ይሄዳሉ እንጂ ልጆቹ ከቤተ ክርስቲያን ማግኘት የሚገባቸውን አያስቡም፡፡ ከቤተ ክርስቲያንና ከጸሎትዋ ጋር ሳይተዋወቅ ያደገ ልጅ ዘወትር በቤተ ክርስቲያን እንግዳ እንደሆነ ይሰማዋል፡፡
- ከአዋቂዎች ይልቅ ልጆች ቤተ ክርስቲያን ታስፈልጋቸዋለችና በልጅነታቸው ዕድሜ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድን አትከልክሉአቸው፡፡
- መንፈሳዊ ቅዝቃዜን እንጂ በቅዝቃዜ ወቅት፣ በዘላለም እሳት መሰቃየትን እንጂ በሙቀት ወቅት ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድን አትፍሩ፡፡
- ፈጥናችሁ ኃጢአት መሥራትን አስወግዱ እንጂ በማለዳ ወደ ቤተ ክርስቲያን መገስገስን አታስታጉሉ፡፡
- ለጸሎትና ለምስጋና በቤተ ክርስቲያን መዘግየትን ሳይሆን ቴሌቪዥን ለማየት ወይም ለዓለማዊ ነገር ማምሸትን አስወግዱ፡፡
- አስቀድመን በልጆቻችን ሕይወት ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን ካልተከልናት በወደፊት ሕይወታቸው የጽድቅን ፍሬ ሊሰጡ አይችሉም፡፡

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- ልጆቻችን የመንፈስቅዱስን ሥራና ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ምስጢራት አማካይነት ከልጅነታቸው ጀምሮ እንዲሳተፉ ካላደረግናቸው በሕይወታቸው የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ እያየን እንድንደሰት ሊያደርጉን አይችሉም፡፡ ለምሳሌ የፍቅርን፣ የደስታ ሳቅን፣ የሰላምን ነገር በልቦናቸው ልናገኝ አንችልም፡፡ ‹‹የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው፡፡›› *<u>ገላ 5፡22፡፡</u>*
- ቤተ ክርስቲያን ቤታችን፣ የአባታችን የእግዚአብሔር ቤት፣ ቅዱሳንና መላእክት የሚገኙባት በምድር የምትገኝ ሰማያዊት መንግሥት ናትና ይህን የእንግድነት ስሜትን ከውስጣችን አውጥተን እንጣለው፡፡
- የሕይወት ምንጭ የሚያልፈው በርስዋ በቤተ ክርስቲያን ስለሆነ በዚህ ወንዝ አጠገብ ልጆቹን የሚያሳድግ ሁሉ ‹‹እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፥ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል፡፡›› *<u>መዝ 1፡3፡፡</u>*
- ‹‹ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች፡፡›› *<u>ማቴ 21፡13፡፡</u>* እንዳለን በእውነት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ናት፡፡
- ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት የሠራተኞቹ አለቃና ‹‹በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡፡›› *<u>ማቴ 16፡18፡፡</u>* ያለ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

## 2. <u>ኦርቶዶክሳዊው ሰው - እንደ አድማጭ በቤተ ክርስቲያን</u>

- የገጠመንን ነገር ለማድረግ ያህል ከልብ ላንሰማና ላንሳተፍ ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንመጣ ከሆንን መንፈሳውያን የሆኑ ስጦታዎችን በመቀበል የሚገኘውን ደስታ እናጣለን፡፡

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- ይህም የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንድንጠይቅ ያስገድደናል፡፡
  - ለመጸለይ ሳይሆን ለማዳመጥ ሲሉ ብቻ ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ የሚያደርጋቸው ምንድር ነው?
  - አድማጭ ብቻ የሆኑ ሰዎች እንዴት ይታወቃሉ?
  - ይህን ዓይነት ግኑኝነት መጨረሻው ምንድር ነው?
- መንፈሳዊውን አገልግሎት ከልብ እንዳንሰማ የሚያደርጉ ምክንያቶች
  - ዘወትር የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተሳታፊ አለመሆናችን፣ ወላጆቻችን ወደ ሰንበት ት/ቤት የማይወስዱን መሆናቸው፣ ይህን ወደ መሰሉ መርሐ ግብሮች አለመምጣታችን፣ ቅዳሴ አለማስቀደሳችን…
  - የቤተ ክርስቲያንን ዜማዎች፣ መዝሙራቱን፣ ግዕዝን አለማጥናታችን፤ ጣፋጭነታቸውን ባለመቅመሳችን የተነሳ ጸሎቱን ስንሰማ ልባችንና ስሜታችን ጥልቅ በሆነው የምስጋና ሕይወት ባለመመሰጡ
  - በትንቢተ <u>*ኢሳይያስ 15፡8*</u> ‹‹ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ፡፡ሕዝቡንም ጠርቶ፡፡ ስሙ አስተውሉም፡፡›› በማለት እግዚአብሔር እንደተናገረው በአካል ወደ ቤተ ክርስቲያን ብንሄድም ልባችንና አእምሮአችን ከዚህ ዓለም በሆኑ ነገሮች በመታጠሩ

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- ከልብ እንዳንሰማ የሚያደርጉ ምክንያቶች…
  - ስለ ኃጢአታችን ንስሐ ባለመግባታችን የሰማያት ደጆች ስለተዘጉብን፡፡ ኃጢአት በእግዚአብሔርና በእኛ መካከል የልዩነት ግድግዳን የሚያኖር ስለሆነ ንስሐ መግባትና በጸሎትም መታደስ ያስፈልገናል፡፡
  - ልባችን እንደ መለኮት ፈቃድ ባለመሆኑ እግዚአብሔር የሰጠን ፍቅር ስሜት አልሰማ ስላለን፤ የሚወደውን እንጠላለን የሚጠላውን እንወዳለን በዚህም የተነሳ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሳናደርግ እንገኛለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ወንድሙንም የሚወድ በብርሃን ይኖራል ማሰናከያም የለበትም፤ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ፥ በጨለማም ይመላለሳል፥ የሚሄድበትንም አያውቅም፥ ጨለማው ዓይኖቹን አሳውሮታልና፡፡›› *ቀዳ ዮሐ 2፡10-11* እንዳለ፡፡
- የተወደዳችሁ ምዕመናን! ሕይወታችንን በምድር ባለች የእግዚአብሔር መንግሥት - በቤተ ክርስቲያን መትከል ይገባናል፡፡ ልጆቻችንን የቤተ ክርስቲያንን ዜማ እንዲያውቁ እናድርጋቸው፡፡ እኛ ካልተማርን አሁን እንማር፤ እንዲህ በማድረጋችን ራሳችንንም ሆነ ቤተሰቦቻችንን እንጠቅማለንና፡፡
- የበዓላት ዕለታትን እንደ አጋጣሚ በመጠቀም መዝሙረ ዳዊትን፣ ውዳሴ ማርያምን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እንዲደያጠኑ እናድርጋቸው፡፡
- ወላጆች ሆይ! ልጆቻችን የንስሐን ሕይወት እንዲለማመዱ እንዲዋሐዳቸውም አናድርጋቸው፡፡ ድንግልናቸውንና ንጽሕናቸውን እንዲጠብቁና ልቦናቸውም የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ ወደሚረዱአቸው፣ ወደንስሐ አባቶች እንዲቀርቡ እናድርጋቸው፡፡

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- ከልብ የማይሰሙ ሰዎች እንዴት ያሉ ናቸው?
  - በተቻለ መጠን አጭር ጊዜ ለመቆየት አስበው ዘግይተው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡና አገልግሎቱ ሳይጠናቀቅ ቀድመው የሚወጡ፡፡
  - ቅዳሴ ተሰጥዖ የማይቀበሉ ወይም በጸሎት ጊዜ የድርሻቸውን ምላሽ የማይሰጡ፡፡
  - ወደ ምሥዋዑ ተመስጦ የማያደርጉ፣ መረጋጋት ያጡ፣ ግራ ቀኛቸውን ዝም ብለው የሚቃኙ፣ ደጋግመው ሰዓታቸውን የሚመለከቱ
  - በዙሪያቸው እየተደረገ ላለው አትኩሮት የሌላቸው (ሰው ሁሉ ቆሞ የሚቀመጡ)፣ ምዕመናኑ ሁሉ አትኩሮታቸው ወደጸሎት ሆኖ ሳለ ልባቸውና ዓይናቸው ከቤተ ክርስቲያን ውጪ የሆነውን (ቤትን፣ ሥራን፣ ገንዘብን) የሚያስብ ወዳልሆነውም የሚመለከት
- አድማጭ ቢያዳምጥም በልቡ ውስጥ ግን የሚያስቀረው፣ ስሜቱን የሚነካ ምንም ነገር የሌለው ነው፡፡
- የአድማጭ ጸሎቱ ከከንፈር እንጂ ከልብ የሚመነጭ ስላልሆነ ቅድመ እግዚአብሔር አይደርስለትም፡፡
- ከልብ የሆነ ጸሎት ግን ፈጥኖ ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል፡፡
- አድማጭ ‹‹አቤቱ፥ አንተን ከጥልቅ ጠራሁህ፡፡አቤቱ፥ ድምፄን ስማ ጆሮህ የልመናዬን ቃል የሚያደምጥ ይሁን፡፡›› *መዝ 129(130)፡1-2፡፡* እንዳለ ልበ አምላክ ዳዊት ማለት አይቻለውም፡፡

## 3. ኦርቶዶክሳዊው ሰው - በቤተ ክርስቲያን እንደሚጸልይ ሰው

- ከቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወታችን መጠቀም ከፈለግን እንደ እንግዳና አድማጭ ሳንሆን ከጸሎትዋ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- በቤተ ክርስቲያን ቅዳሴን ማስቀደስ ወደ ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም በሚደረግ ጉዞ እንደመሳተፍ ነው፡፡ ዝግጅቱም በቤት ተጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ይጠናቀቃል፡፡ በመለኮታዊው ዙፋን ፊት ለመቆም ልባችንንና አእምሮአችንን በቤታችን አዘጋጅተን ብንቀርብ ይህ ዕለት ልዩ ዕለት ይሆንልናል፡፡ እኛና ቤተሰቦቻችንም የሠርኩን ጸሎትም መሳተፍ ይገባናል፡፡ እንግዲህ ልቦናችንና አካላችን ንጹሕ መሆኑን አረጋግጠን ለሥጋዊ ሳይሆን ለሰማያዊ ደስታ ራሳችንን እናዘጋጅ፡፡
- በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ ዝግጅቶች በጸሎትና በንባብ ተጀምረው ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል ከጌታችን ጋር መኖር የምንችልበትን ዕድል አስገኝተው ይፈጸማሉ፡፡
- ጥልቅ በሆነው ጸሎት ደስ ለመሰኘት የሚከተሉትን ይዘን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ፡፡

**በደስታና ከፊት ይልቅ በበረታ ቀጥተኛነት ወደ ቤተ ክርስቲያን አንገስግስ**

- በደስታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ብንገሰግስ በልበ አምላክ ዳዊት ‹‹ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሄድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ፡፡›› *መዝ 121(122)፡1*፣ ‹‹ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች ትወድዳለች ትናፍቅማለች ልቤም ሥጋዬም በሕያው አምላክ ደስ ተሰኙ፡፡›› *መዝ 83(84)፡2፡፡* ማለት ይቻለናል፡፡
- ወደ ቤተ ክርስቲያን የምንገሰግሰው መንፈሳዊ በረከትን ፈልገን ነው፤ እግዚአብሔርን የምናየው በውስጥዋ ፣ ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል ከእርሱ የምንዋሐደው በርስዋ ነውና፡፡
- እግዚአብሔር በመካከላችን ነው፣ በቤተ ክርስቲያንም ለደቀመዛሙርቱ በደብረ ታቦር እንደተገለጠላቸው በቤተክርስቲያን ደስ በሚያሰኝ መንፈሳዊ ኃይል ዘወትር ይገለጣልና፡፡

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ቢገናኝ ፊቱ እንደፀሐይ አብርቷል፡፡ አምላካችንም በምንቀበለው ቅዱስ ቁርባን ራሱን ገልጦልናል፤ በምንቀበለውም በዚህ (ቁርባን) ብርሃን ለዓለሙ ሁሉ ብርሃን እንሆናለን፡፡
- በቤተ ክርስቲያን ‹‹ከኃይል ወደ ኃይል ይሄዳሉ የአማልክት አምላክ በጽዮን ይታያል፡፡›› መዝ <u>*84(85)፡7፡፡*</u> እንደተባልን መንፈሳዊ ኃይልን እናገኛለን፡፡
- በዚህም ኃይል ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ፡፡›› <u>*ፊል 4፡13፡፡*</u> በማለት እንደጻፈልን አባቶቻችን ሐዋርያት በመከራው ሁሉ ጸንተዋል፡፡
- በሕይወታችን ይረዳን ዘንድ በቤተ ክርስቲያን በምንማረው መንፈሳዊ ትምህርት አማካይነት እንበረታለን፡፡ ‹‹በመከራ ቀን እግዚአብሔር ይስማህ የያዕቆብ አምላክ ስም ያቁምህ፡፡›› <u>*መዝ 20፡1፡፡*</u> እንደተባለ ለእኛ በሚጸልዩ በአባቶቻችን ሊቃነ ጳጳሳትና በቀሳውስት እንዲሁም በዲያቆናትና በምዕመናን ጸሎት ስንጮህ እግዚአብሔር ይመልስልናል፡፡
- ጌታችን ‹‹ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል፡፡›› <u>*ዮሐ 6፡57፡፡*</u> በማለት እንደነገረን በምንቀበለውም ቅዱስ ቁርባን የሚበልጥ ኃይል እናገኛለን፡፡

## በማለዳ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንገስግስ

- አምላካችን እግዚአብሔር ‹‹እኔ የሚወድዱኝን እወድዳለሁ፥ ተግተው የሚሹኝም ያገኙኛል፡፡›› <u>*ምሳ 8፡17*</u> በማለት ይናገረናል፡፡

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ወደ ጌታችን መቃብር በማለዳ በመገስገሳቸው የትንሣኤው ደስታ ተካፋይ ለመሆን በቅተዋል፡፡ መግደላዊት ማርያምና ሌላይቱ ማርያምም ከትንሣኤው በኋላ ከጌታችን ጋር በመነጋገር ለመደሰት ቀዳሚ ነበሩ፡፡ ለደቀመዛሙርቱም እንዲነግሩ የላካቸው እነርሱን ነበር፡፡ ማቴ 28፡10፡፡
- ልበ አምላክ ዳዊት ‹‹አምላኬ፥ አምላኬ፥ ወደ አንተ እገሠግሣለሁ ነፍሴ አንተን ተጠማች፥ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች እንጨትና ውኃ በሌለበት በምድረ በዳ፡፡›› መዝ 62(63)፡1፡፡ ብሎናል፡፡
- ወንጌል ከተነበበ በኋላ ደርሰን ቅዱስ ቁርባን ልንቀበል ስንሞክር ቤተ ክርስቲያን የምትከለክለን መራር ስለሆነችብን ሳይሆን ከቅዳሴው መጀመሪያ ጀምሮ ባለው ሰማያዊ ጉዞ ደስ እንድንሰኝ ስለወደደች ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን የተቀደሰ ቤተ መቅደስ ሆነን እንድንዘጋጅ ጸሎቱንና ምንባቡን ሁሉ እንድንሰማና ታላቅ መንፈሳዊ ኃይል ተሰምቶን ደስ እንድንሰኝ ትሻለች፡፡

**ለንስሐ በተዘጋጀ ልቦና ወደ ቤተ ክርስቲያን እንግባ**

- ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንገሰግስ ‹‹አቤቱ፥ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል? በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል?›› መዝ 15፡1፡፡ ብንል እግዚአብሔር ‹‹በቅንነት የሚሄድ፥ ጽድቅንም የሚያደርግ፥ በልቡም እውነትን የሚናገር፡፡በአንደበቱ የማይሸነግል፥ በባልንጀራው ላይ ክፋትን የማያደርግ፥ ዘመዶቹንም የማይሰድብ፡፡ኃጢአተኛ በፊቱ የተናቀ፥ እግዚአብሔርንም የሚፈሩትን የሚያከብር፥ ለባልንጀራው የሚምል የማይከዳም፡፡ገንዘቡን በአራጣ የማያበድር፥ በንጹሑ ላይ መማለጃን የማይቀበል፡፡ እንዲህ የሚያደርግ ለዘላለም አይታወክም፡፡›› መዝ 15፡2-5፡፡ በማለት ይመልስልናል፡፡
- ይህን ጸሎት ስንጸልይ በሕይወታችን ይንጸባረቃል? የሚታይስ የንስሐ ሕይወት አለን?

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- ወደ ቤተ ክርስቲያን ‹‹እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ አንተን በመፍራት ወደ ቅድስናህ መቅደስ እሰግዳለሁ።›› እያልን በተሰበረ ልብ እንቅረብ። *መዝ 5፡7።* በንስሐም ‹‹በልብዋ። ልብሱን ብቻ የዳሰስሁ እንደ ሆነ፥ እድናለሁ ትል ነበረችና።›› እንደተባለችው ሴት በመንበሩ ፊት በሥላሴ ፊት እንስገድ።
- በመንበሩ (በሰማያዊ ዙፋኑ) ወዳለው፣ መንፈሳዊ ዝለታችንን ሊያክም ወደሚቻለው ወደ አምላካችን እግዚአብሔር ኃይሉን ይሰጠን ዘንድ በጸሎት እንጠይቅ።
- በዚህ የንስሐ ሕይወት ከቀረብን ካህኑ ‹‹እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ›› ብሎ የሚጸልየውን ጸሎት ስንሰማ ኃጢአታችን ይታሰበናል። እንዲሁም ካህኑ ‹‹12 ጊዜ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ በሉ… 12 ጊዜ በእንተ እግዝእትነ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ በሉ›› ሲሉን ጌታችን በሰውነቱ ላይ የቆሰለው ቁስል እንዲሁም የበዛ ኃጢአታችን ይታወሰናል።
- ካህኑ ‹‹ቅድሳት ለቅዱሳን›› ሲል ቅዱስ ቁርባንን (ቅድሳቱን) እንዳንቀበል የለየንና ያራቀን ኃጢአታችን እንደሆነ ይታወሰናል። ስለዚህ በመዝሙረኛው በዳዊት ‹‹በሂሶጵ እርጨኝ፥ እነጻማለሁ እጠበኝ፥ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ።›› *መዝ 50(51)፡7።* እንበል።

**ፍጹም በሆነ አክብሮት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንግባ**

- ያዕቆብ ‹‹ፈራ፥እንዲህም አለ፦ ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራ ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም ይህም የሰማይ ደጅ ነው።›› *ዘፍጥ 28፡17።* አለ እንደተባለ በመፍራት ወደ ቤቱ እንግባ። ጸሎታችንን እግዚአብሔርን በመፍራት እናቀርብ ዘንድ በቤተ ክርስቲያን የምንቆመው በየት ነው? የሚገቡና የሚወጡ ሰዎችን ማየት በሚመመስችለን ቦታ ነው? ቅዝቃዜን ወይም ሙቀትን ልናገኝ በምንችልበት ሥፍራ ነው? ወይስ ጓደኞቻችን በሚሰባሰቡበት?

# <u>በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን</u>

- የተወደዳችሁ ምዕመናን ሆይ! ከቅዱስ እግዚአብሔር ጋር በፍጹም ተመስጦ መገናኘት ያስችለን ዘንድ በቅርባችን ከምናውቃቸው ተለይተን እንቁም።
- የምንቆመው በእግዚአብሔር ፊት ነውና ከክብሩ የተነሳ ፊታቸውን በክንፋቸው የሚሸፍኑ ሱራፌልን ሆነን በፊቱ እንቁም። ስንጸልይም ዲያቆኑ እንደሚነግረን በመፍራትና በፍጹም አክብሮት ቆመን እንጸልይ። *<u>ኢሳ 6።</u>*
- መንፈስቅዱስ በምስዋዑ ላይ በሚወርድበት ጊዜ እኛ መቀመጥ እንዴት ይሆንልናል? ካህናት ለአገልግሎት መነጋገር ቢያስፈልጋቸው እንኳ በምልክት እንደሚጠቀሙ እናድርግ። ዲያቆናቱም ስለድምጻቸው ማማር ተመክተው ዜማውን ሁሉ በማዳነቅ ከሌላው ድምጽ አጉልተው ወይም ጎትተው እንዳይገኙ ይገባቸዋል፤ ይህ ሁሉ ለእግዚአብሔር ከምንሰጠው ክብር ጋር ይጋጫልና።
- አለባበሳችንም ሥርዓት ያለው መሆን ይገባዋል። ወደ ቤተ ክርስቲያን በተሰበረ መንፈስ ሆነን ይቅርታን ለማግኘት፣ መዳናችንን ሽተን መንግስተ ሰማያትን ለመውረስ እንጂ ፋሽን ለማሳየት አንመጣምና።

## 4. <u>ኦርቶዶክሳዊው ሰው - በቤተ ክርስቲያን እንደሚያገለግል ሰው</u>

- በቤተ ክርስቲያን ያለ አገልግሎት ያለጥርጥር በረከት የምናገኝበትና ከእግዚአብሔርም የተሰጠ ነው።
    - አገልግሎት ‹‹ከቶ ለማን ብሎአል? ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?›› *<u>ዕብ 1፡14።</u>* እንደተባለ የመላእክት አገልግሎት ነው።
    - አገልግሎት ወደ ታላቅ ማዕረግ መሸጋገሪያ መንገድ ነው። ‹‹በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን።›› *<u>ማቴ 20፡26።</u>*
    - አገልግሎት ከፍ የሚመመደርግ የሚያሳድገንም ነው። ‹‹ከእናንተም የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሆናል ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፥ ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ይላል።›› *<u>ማቴ 23፡11-12።</u>*

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- አገልግሎት ‹‹እንደዚህ አድርጎ ለክርስቶስ የሚገዛ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛልና፥ በሰውም ዘንድ የተመሰገነ ነው።›› *ሮሜ 14፡18።* እንደተባለ እግዚአብሔርን ደስ የምናሰኝበት ነው።

- ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹እግዚአብሔር፥ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና።›› *ዕብ 6፡10።* በማለት እንደተናገረው በአገልግሎት ክብር እናገኛለን። ‹‹የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፥ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል፤ የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል።›› *ዮሐ 12፡26።*
- አገልግሎት በምድር ብቻ የተሰጠን ክብርና በረከት ሳይሆን ሰማያዊ በረከትና ክብር ነውና በማገልገላችን ሰማያዊ ክብርና በረከት እናገኛለን። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያረጋግጥልን ‹‹ከጌታ የርስትን ብድራት እንድትቀበሉ ታውቃላችሁና። የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነውና።›› *ቆላ 3፡24።* እንዳለን።
- የተወደዳችሁ ምዕመናን! በማገልገል ስለሚገኘው በረከት ከሰማችሁ እናንተና ቤተሰዎቻችሁ ሁሉ ለማገልገል አልጓጓችሁም? ምናልባት ለማገልገል ፈልጋችሁ ትክክለኛው ችሎታ የሌላችሁ ሆኖ ተሰምቷችኋል? ለምሳሌ ማስተማር አልችልም፣ ለመዘመር የሚያስችል ድምጽ የለኝም ብለን ይሆናል። ነገር ግን በርካታ የምንሠራው ሥራ በቤቱ እንዳለና እንደተዘጋጀልን እንወቅ። የሰውን አካል እያንዳንዱን ብልት፣ ሴሎቹን ተመልከቱ፤ እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ሥራና ድርሻ አላቸው።
  - እያንዳንዱ ሥራ ብቸኛና ያንም የሚሠራ የተወሰነ አካል አለው። ለምሳሌ የልብ ሥራ ከአእምሮ ወይም ከጉበት ሥራ ይለያል።
  - ሥራው እጅ/እግር እንደሚንቀሳቀስ የሚታይ ወይም እንደልብና አእምሮ ሥራ የማይታይ ሊሆን ይችላል። ከሚታየው ይልቅ የማይታየውም አካል ሥራ ጥልቅ እንደሆነ ልብ እንበል!

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

- የአንዱን ሥራ ከሌላው እጅግ ተፈላጊ የሌላውንም የማይፈለግ ማድረግ የለብንም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም አካላት በአንድነት ለመላው ሰውነታችን ጥቅም ይሠራሉና፡፡
- ሁሉም አካላት የየራሳቸው ሥራ አላቸው፣ ስለዚህም ሕይወት ያላቸውና ተንቀሳቃሽ ናቸው፡፡
- ከአካላቱ የማይሠራ ካለ መላው አካል ሊጎዳና ለሞትም ሊያደርስ ይችላል፡፡ስለዚህም ነው ዶክተሮች ሌላው አካል ጤንነቱ እንዲጠበቅ የታመመውን የተበላሸውን አካል ቆርጠው የሚጥሉት(Amputation)፡፡

- እንደዚሁ እያንዳንዱ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን በአንድዋ አካል በቤተ ክርስቲያን ሕያው ሆኖ የሚኖር አካል ነው፡፡ ራሱም የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነ ክርስቶስ ነው፡፡ ‹‹ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?›› ***ቀዳ ቆሮ 6፡15፣ ኤፌ 5፡30፡፡***
- እያንዳንዳችንም እንደችሎታችን የተለያየ ድርሻ አለን፡፡ ‹‹በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፥ የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ፥እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን፡፡እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤ ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤ የሚምር በደስታ ይማር፡፡›› ***ሮሜ 12፡4-6፡፡***
- ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን እንደ ማንነታችንና እንደ ድርሻችን በርካታ አገልግሎት እንዳለ እንወቅ፡፡

# በቤተክርስቲያን የምትኖር ቤታችን

**መንፈሳዊ አገልግሎት**

- **ማስተማር፡-** ይህ ከልጅነታችን ጀምሮ ለአገልግሎት የሚያበቃንን ትምህርት መማር ይፈልጋል።
- **የቤተ ክርስቲያናችን ያሬዳዊ ዜማ፡-** ልጆቻችንን ከልጅነታቸው ጀምሮ ያሬዳዊ ዜማን፣ የቤተ ክርስቲያንን መዝሙራት እንዲያጠኑ፣ ቅዳሴ ተሰጥኦ እንዲያውቁ… እናድርጋቸው። በዚህም አካሄዳቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ ታውቀው ቤተ ክርስቲያንም አውቃቸው የሚያገለግሉበት መሥመር ተገልጾላቸው፣ ተፈቅዶላቸው ያድጋሉ።
- **ጸሎት፡-** በቤተ ክርስቲያን የሠርክ ጸሎት፣ በመንፈሳዊ ስብሰባዎች በመሳተፍ በዚህም የሚያስፈልገውን በማበርከት ያድጋል ይበለጽጋል።

**ማኅበራዊ አገልግሎት**

- ሕሙማንን መጠየቅ ሕሙማንን ማገልገል (እመቤበታችን እንዳስተማረችን - ሉቃ 1፡39-)፣ እስረኞችን መጠየቅ፣ የሰንበት ተማሪ ወጣቶችን ወላጆች እየተገናኙ ስለሕይወታቸው መሻሻል መመካከር…

**የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት**

- ቤተ ክርስቲያን ከልጆችዋ አስተዳደራዊ ሥራዎችን የሚያደራጁላትን፣ አጋዥ ፕሮጀክቶችን የሚያጠኑላትን… ትፈልጋለች።
- የቤተክርስቲያን አገልግሎት ሰፊ ስለሆነ ሕይወት ያለን ሆነን መኖር የሚያስችለንን - የሚመጥነንን እንምረጥ። ቅዱስ ጳውሎስ የሰጠንንም ምክር ሳንረሳ ‹‹ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ።›› ሮሜ 6፡13። ልጆቻችንም ፈለጋችንን እንዲከተሉ እናድርጋቸው

# ይቆየን።

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org